# የታላቁ ውይይት ውጤት በሲያትል

December 27, 2015

በዘውገ ፋንታ
zegfanta@outlook.com



በጉጉት ይጠበቅ የነበረው የኢትዪጵያ ወገኖች በስያትል ውይየት በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ አልፏል። የክብር እንግዶች ዶ/ር ጌታቸው፣ ዶ/ር አስክየል፣ እና ዶ/ር አሸናፊ ተገኝተው የኢትዮጵያን ሕዝብ ጉዳይና ጊዜአዊ ችግር በሚገባ አንጸባርቀዋል። በዚሁ ቀን ከሕዝቡ መካከል አንድ ታላቅ አባትና መሪ የሆኑ አቶ አደም ተወለዱ ወይም ደረሱ ቢባል ተራ የቃል ምርጫ ሳይሆን ለኢትዮጵያ አዲስ ታሪክ ሂደት ትክክል መልዕክት ነው ብሎ በማመን ነው። አቶ አደም ከወያኔ በኋላ ለምትገነባው አዲሲቱ ኢትዮጵያ የሚውል መሪ ቃልና የኢትዮጵያን ባሕሪና ስርዓት የሚገነባ ልቦና አስተጋብተዋል። የዚህ ጽሑፍ ዋናው ከፊሉ ዓላማም የኒህን ታላቅ አባት ድምጽና ምክር ለማስተጋባት ነው። አቶ አደም የጃጋማ ኬሎና የኮሎኔል ዓለሙ ቂጤሳ እንዲሁም ከነሱ በፊት ለነበሩት የኢትዮጵያ ግንዶች የዘመኑ የኢትዮጵያ መድኽን ቃል አስተጋቢ ሁነው ባስፈላጊውና በጭንቁ የኢትዮጵያ ወቅት የዘለቁ (የተወለዱ ቢባል) ትክክል ይሆናል። ኢትዮጵያ ዘላቂና ዘላለም ኗሪ ሀገርና ሕዝብ መሆኑን በአቶ አደም ተረጋግጧል። በዚሁ ዕለት ሌሎችም አባቶች ኢትዮጵያና ሕዝቧ ጠርቷቸው ብቅ ያሉ አውታሮችና ግንዶች መድረኩን ማርከው ይዘው ነበር። አቶ ገብረሥላሴ የኢትዮጵያን ሕዝብ አጠቃላይ ችግር በዚህ ታሪካዊ መድረክ የተገኘው የኢትዮጵያ ወገን ከውስጡ ገብቶ ፈልፍሎ ችግሩን እንዲረዳ አድርገዋል። ተበዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየወንዙና ጎራው ያለው እንዲታወስና ያላወቀውና ያልሰማው በወንዝ ወዲያ ማዶ ያለው እንዲስማና እንዲሰማማ አድርገዋል። በስብሰባ የተገኙት ልጆቻቸው ዕድሜአቸውን ሙሉ ሲጨነቁበት የነበረውና መፍትሔ ያጡበት ጉዳይ፣ በድንገት ባልጠበቁበት ወቅት ከአባቶቻቸው የሰሙት ዕንቁ መሪ ቃል በዕንባ ትንቅንቅ ጋር ከሕዝብ ፊት ቆመው ገልጸዋል። እንኳን ውጭ ላለው ከሀገር ውስጥ ላለው ታላቁ ወገንም እጅግ የሚያስንቅ ታሪካዊ ንግግርና ራዕይ የሚገነባ መሪ ቃሎች ተንጸባርቋል። ከላይ የተጠቀሱት ታሪካዊ ቃሎች ለዓለም መሰራጨት አለባቸው። ለመስማት ብቻ ሳይሆን፣ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ መገንቢያ የሚሆኑትን ማዕዘንና ምሰሶ አጥብቀው እንዲረዱ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባርኮ ያከብራቸውና፣ በእንግዳ ለውይይት የተገኙት ምሑራኖች ፐ/ር ጌታቸው፣ ዶ/ር እስቅየልና ዶ/ር አሸናፊ የነዚህን የአበው ቃል ድምቀትና ታላቅ ቦታ እንዲሰጠው ለማድረግ ተማጽነው አድናቆታቸውንና አክብሮታቸውን አጉልተው ገልጸዋል። ቃል ሊገልጸው የማይችል ስሜት በአዳራሹ ታይቷል። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ይኽ የመጀመሪያው ዕውነተኛ የኢትዮጵያኖች ስብስብ መሆኑና በውጤቱም ኢትዮጵያኖች በመንፈሳቸውና በአስተሳሰባቸው ብዙ ዓመት ታራምዶ እንዲሄድ ያደረገ ውይይት መሆኑን በምስክርነት ሲያቀርብ ያለ ማወላወል በታላቅ ኩራትና ደስታ ነው።

ይኼንን ሁኔታ ያፈለቀውና ያስተናገደው የምሁራኖቹ አቀራረብ ነበር ቢባል ተገቢና ትክክል ነው። የውይይቱ መነሻና መነጋገሪያ የሆነው / የነበረው በቅርቡ የኢዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ በተነሳበት ነፍስ በወደመበት 'የአዲስ አበባ የከተማ ስፋት ዕቅድ' በተባለው ይኼው አወናባጅ መንግሥት በፈጠረው ጉዳይ ላይ ነበር። አቶ ቢተው (የሰብሳቢው ኮሚቴ) አስተናጋጅ አስቀድሞ መግለጫ አቀረበ። ስለ አቶ ቢተው ጠቀም ያለ አስተዋጽዖ በኋላ ይገለጻል። ሶስቱ ምሑሮች በተከታታይ ያቀረቡት ስለ ከተማው ስፋት ዕቅድ ውጣ ውረዱን አስመልክቶ ዶ/ር አሸናፊ፤ ሰለ አዲስ አበባና አካባቢ ጥንታዊ ታሪክና ዝልቀት ዶ/ር እስቂየል፤ በመጨረሻም ዶ/ር ጌታቸው የሕዝብን መሻሻልንና የሀገር ወይም ክፍለ ግዛትን አስመልክቶ ለሚሆነው ዕድገት በተሳኑበት በኢኮኖሚ ምርምር አንጻር እሳቸውም በዚህ ላይ እንዲሁ ሰፊ መግለጫ አቀረቡ። ባጭሩ የሶስቱም መልዕክት ይኼን ይመስል ነበር።

ዶ/ር አሸናፊ ከቀድሞው የአዲስ አበባ (አ. አ.) የከተማ ስፋት ዕቅድና ስልት እሳቸው የተሳተፉበትን የቀድሞ ዕቅድ (ሳይሰራበት ከሽፎ የቀረውን) እንዴት እንደተጀመረና የነበረውን ውጣ ውረድ የዎያኔ ውጥንቅጥ አካሄድና ፖለቲካዊ በሆነ አመራር የደረሰውን ቀውስ በሚገባ አስረዱ። ዶ/ር አሸናፊ ለሀገር ዕድገት የተነሱትን ምሑራኖች ወኒ ቀስም የሚሰብረውን የዎያኔን አዳጋች ባሕሪ በሚገባ አድርገው ገለጹ። ዎያኔዎች የዕቅድን ጥቅምና አስፈላጊነት በሚገባ የማያውቁ በመሆናቸው፣ የሚከተሉትና የሚወዱት የአሰራር ሂደት፣ አንደኛ ራሳቸውን እና አባሮቻቸውን የሚጠቀሙበት ስልት ሆኖ ሲያዩት፤ ሁለተኛ፣ ቸብ ቸብ ተደርጎ ለዐይን እንዲታይ ከመሬት በላይ ለሚቆመው ግንብ እንጂ (በዚህ ጸሐፊ ቃል ገለጻ፣ 'የዕምቧይ ካብ) ለዛሬ ውይም ለነገ ትውልድ ለሚሆን ውል ስራ አለመሆኑን ምሑሩ በሰፊው ገለጹ። ዶ/ር እሸናፊ ያሁኑን ችግር ከዚሁ የዎያኔ ጥቅም የተያያዘ መሆኑን ማስረጃውን በማሳየት፣ የሕዝቡ ጥያቄና ለግድያ ያበቃውን መሰረታዊ ችግር ተንትነው በማቅረብ፣ ገበሬው የተዘረፈውን ዎያኔዎች እንዴት እንደከበሩበትና ይኼንኑ ስልት በመቀጠላቸው ሕዝብ በቃኝ በማለት ከዳር እስከ ዳር ተባብሮ መነሳቱን እጥብቀው አስረዱ። የጥቅሙን ተዘላላፊነት ሲያስረዱ፣ ለገበሬው በካሪ ሜትር በሳንቲም ልክ የከፈሉበትን መልሰው በብዙ ሺህ ብር እየሸጡ ዎያኒዎች እየከበሩ ያሉበትን ስልት ዶ/ር አሸናፊ ዘርዝረው አቀረቡ። ተሰብሳቢው ሕዝብ

ይህንን አጸያፊና አረመኔ ምግባር ሰምቶ ከግድግዳ እስከ ግድግዳ በንዴትና በመገረም ከንፈሩን ሲመጥ ተሰምቷል። የኢትዮጵዮ ሕዝብም በቃን ብሎ የተነሳው ይኼንኑ ግፍ በማየቱና በመስማቱ መሆኑን ዶ/ር አሸናፊ በሚገባ ገለጹ።

ሁለተኛው ተናጋሪ እጅግ ጥልቅ ምርምሮችን ያጠናቀቁና ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረጉ ምሑር ናቸው። የታሪክ ምሑር በመሆናቸው የጊዜው ውዥግብ የተፈጠረበትን መሰረታዊ ጉዳይና ምክንያት ከታርክ አንጻር በሚገባ አድርገው አቀረቡ። ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ እጅግ የሚያኮራ ታሪክ መሆኑን በጭብጨባ አረጋግጧል። አ. አ. ታላላቅ ሰዎች የሰፈሩባት ምድር መሆኗን እስከ አሁን የሚጠሩበትን ስም በሚገባ ገልጸዋል። አ. አ. እየተስፋፋች ስትሄድ የነዚህ ቀድሞ ሰፋሪዎች እርሻም ይሁን ቃየ (የከብት መዋያ ቦታ) መነጠቃቸውን ገልጸዋል። ካሁኑ ችግር ጋር ለማያያዝ የወያኔን ደባ የፖለቲካ ሂደት አጣምረው ገልጸዋል። አንዱ የዎያኔ ዘይቤ አዲስ አበባን በማስፋት ወያኔን ለሁለት ለመቁረጥና የማይገናኙ ምስራቅና ምዕራብ የሚባሉ ሁለት ኦሮምያን ለመፍጠር እንደሆነ አስረዱ። ይኼንንም የፌደራል አወቃቀርና የዕድገት ግዛት (Developmental State) በሚለው መዋቅር ላይ የሚደረግ ግራ-ቀኝ ጉትቻ እንደሆነ ገልጸዋል። ዶ/ር እስቅየል የኦሮሞ ሕዝብ በባህሉ የሚሳለቅበት፣ በኢኮኖሚም የተበደለበትና የሚበደልበት አገዛዝ ስልት መሆኑን ገልጸው፣ የኦሮሞ ሕዝብ ከዚህ ጭቆና እንዲላቀቅና ነጻነቱን አግኝቶ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በእኩልነት እንዲኖር የሕዝቡን ዕርምጃ ተገቢነት በማስገንዘብ ንግግራቸውን ደምድመዋል።

ሶስተኛው ተናጋሪ ለየት ያለ በኢኮኖሚው ጉዳይ ላይ ያተኮረ ሰፊና ጥልቅ የሆነ ገለጻ አቅርበዋል። ያለውን የጊዜውን ችግር ከኢኮኖሚው ጭቆናና በደል በማያያዝ፣ ዎያኔ የተካነበትን ስልት ተንትነው አቅርበዋል። ፐ/ር ጌታቸው ወያኔ ራሱን ለማዳበር ያሚያገለግለውን ዋና ስልት፣ ሕዝብን በመከፋፈል በመሆኑ፣ ይህን ስልቱን ለሃያ አራት ሲጠቀምበት የቆየ መሆኑንና ሲገልጹ፣ ስልጣን ወደ ኗሪው ሕዝብ እጅ እንዳይገባ የራሱን ሰዎች እየመረጥ ለሕዝቡ የማያስቡ ሰዎችን (ተመሳዩ በረከት ስሞን) በስልጣን እያስቀመጠ፣ ሌሎችንም 'የሆድ-ተገዥዎች' በማይችሉት ሙያና ሥልጣን ላይ (ተምሳሌው ፐ/ም ኃይለማርያም) እያስቀመጠ በእጅ አዙር እየገዛ መቆየቱን ተንትነው ገለጹ። አሁንም ጎልቶ የሚታየው ችግር የተለመደው የኃብት መሰብሰቢያ ያደረገው የእህደግ (ዎያኔ) ስልት ያስከተለው ውዥግብ መሆኑን አሳምረው አስረዱ። በኢኮኖሚው ዕድገት ላይ የሆነውን መበላለጥ፣ ዎያኔና የዎያኔ ዘርፍ በሀብት ክምችት ልቆ ሲሄድ፣ ሌላው በርሃብና  በችግር ከዚያም አልፎ በጥይት መደብደቡ ሕዝቡ ያንገፈገፈው መሆኑንና የመጣውን ለመቀበል በአንድነት መነሳቱን በየቦታው የታየውን እንቅስቃሴ እየጠቀሱ በሰፊው ገለጹ። ምንም እንኳን ዎያኔ እስከ አፍንጫው የታጠቀ ቢሆንም፣ ብዙ ወታደር ልብሱን እያወለቀ እያቃጠለ ከወገኑ ጋር አብሮ መቆሙንና ይኼም እየበዛ የሚሄድ ሁኔታ መሆኑን በመጠቆም የወያኔ ቀን በጣት የሚቆጠር መሆኑን አመልክተዋል። በመደምደሚያ ዎያኔ ከውስጡ መሰባበሩንና የመንኮተኮቻው ወቅት መቃረቡን በሥልጣናቱ መካከል ያለውን ትርምስና ውዥንብር ሲያስረዱ ሕዝብ ደጋግሞ አሜን ብሏል።

ከዚህ ስሜት ቀሰቃሽ ንግግን በኋላ፣ ከሚችለው በላይ በደሉንና በወገኑ ላይ የሚደርሰውን የወያኔ አረመኔ ስራ ሰምቶ እጅግ የከነከነው የኢትዮጵያ ወገን፣ ሰምቶና አሮ ከቤቱ እንደወትሮው የሚመለስ ሳይሆን፣ በተራ እየወጣ የልቡን ገልጿል። ውሳኔ የሰጠባቸው ሀሳቦች፣ ከዚህ በኋላ "የለም መራራቅ! የለም አለመግባባት! የለም አለመተባበር! አንድ ነን!" ብለዋል። "የኢትዮጵያ ዘርፎች ነን፣ 'አፍንጫ ቢደማ፣ አይን ያለቅሳል' ኣንደሚባለው፤ በአዲስ አበባ፣ በጎንደር፣ በኢልባቡር፣ በሌላውም ክፍል በወገን ላይ ለሚፈጸመው ሁሉ ጥቃቱ ይሰማናል፣ ሁላችንም ያገባናል!" በማለት፣ እያንዳንዱ ሰው በሰልፍ ቁሞ ደግሞ ደጋግመው ይህንኑ ቃል አስተጋብቷል። አቶ አደም ያቀረቡት ንግግር ሶስቱ እንግዳ ተናጋሪዎች ያቀረቡን አጥፎ ተገኝቷል። የሶስቱን ምሑሮች ሀሳብ ሕይዎት የሰጠው በመሆኑ። የዚህ ጽሑፍ የተዛባ አስተያየት እንዳይባል፣ ሶስቱም ምሑሮች፣ ለነህ አባት ያሳዩት አክብሮት ልብ የሚነካ ስሜት ነበር። "የቃልዎ አሰራጭ እንሆናለን" ሲሉ ቃል ገብተዋል። ሌሎቹም ተናጋሪዎች የአቶ አደምን ኣንዲሁም የአቶ ገብረሥላሴን መንፈስና መልዕክት በአድንቆት ተቀብለዋል።

መደምደሚያ፣

ስያትል የአያሌ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች መቀስቀሻ በመሆን ለብዙ ጊዜ አገልግላለች። ዎያኔም ጠንካራ ደጋፊዎች አሉት። ቅንጅትን ለውድድሩ ያዘጋጀ፣ ከዚያም የቅንጅት መሪዎችና ሌሎቹም ከእስራት እንዲፈቱ አጥብቆ የታገለ የኢትዮጵያ ብርቱ ወገን ያለበት ነበር/ነው። ከሁሉም ጎራ ያላስተናገደው የፖለቲካ ድርጅት የለም ቢባል ትክክል ነው። ስያትል የመጣ የአገር ውስጥና የውጩ የፖለቲካ ድርጅት የአቋሙና የድጋፉ መለኪያው ነበር ቢባል ስህተት አይሆንም። በአለፈው እሑድ የተፈጸመው ውይይት ለኢትዮጵያ ሰላም መንገድ ከዚያም ለታላቁ ብልጽግና ጎዳና ቀያሽ መሆኑን ፍንጭ ማሳየቱን ይኽ ጸሐፊ ያምንበታል። ይህን በማለቱም ለስያትል የኢትዮጵያ ልጆች ከሚችሉት በላይ እንዳልሆነ አጥብቆ ያምናል። ከስያትል የተጀመረው ተቀጣጥሎ ባህር አልፎ ኢትዮጵያ ይደርሳል የሚል ዕምነት በብዙ ወገን ልብ የተንጸባረቀ ሀሳብ እንደሆነ የታየው ያስረዳል። አዘጋጆቹ ሁሉም ስማቸው ከዚህ ባይጨመርም፣ አቶ ሀብታሙ፣ ዮሐንስ፣ ንግሥትና ሌሎቹም በእጅጉ መመስገን ይገባዋል። አቶ ሀብታሙ የአቶ አደምን ንግግር የተረጎመ ሲሆን በጥረቱ እጅግ ከፍ ተደርጎ መመስገን ያለበት ሰው ነው።